የመዝናኛ፣ ፓርኮችና የባህል ተግባሮች

የፋይናንስ ፖሊሲዎችና ሥነ ሥርአቶች

# የፋይናንስ ድጋፍ

በከተማ ካውንስል XXX የፀደቀ

| | |
|---|---|
| የረቂቅ ቀን | 6/11/2019 ዓ.ም |
| የተፈቀደበት ቀን | 7/01/2019 ዓ.ም |
| የዳይሬክተር ፊርማ | [ፊርማ ] |
| የመጀመሪያ የግንኙነት ሰራተኛ | የRPCA ዳይሬክተር |

## ክፍል 1 – በRPCA ስፖንሰር የሚደረጉ ፕሮግራሞች

### ማጠቃለያ

መምሪያው የነዋሪዎችን በከተማዋ ፕሮግራሞች ላይ መሳተፍ ያበረታታል። የፋይናንስ ድጋፍ ፖሊሲና አሰራር የተዘጋጀው በከተማዋ ፕሮግራሞች ከፍተኛ የነዋሪዎች ተሳትፎ ለማግኘት እንዲያስገኝልን ታስቦ ነው።

### ብቁነት

ሁሉም የብቁነት ደረጃዎችን የሚያሟሉ የከተማዋ ነዋሪዎች ብቁ ናቸው። በሀብት ምደባና የወጪ ማስመለስ ፖሊሲ ከደረጃ 1-4 ስር የሚገኙ ሁሉም የከተማዋ ፕሮግራሞች የፋይናንስ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ ናቸው

### ፖሊሲ የፋይናንስ ድጋፍ በሚከተለው መርሀግብር መሰረት ሊሰጥ ይችላል፡

- በአሌክሳንደሪያ ከተማ ትምህርት ቤት የምሳ ክፍያ ወይም ቅናሽ የሚያገኝ ልጅ ያላቸው ቤተሰቦች 40% ቅናሽ ይደረግላቸዋል።
- የምሳ ክፍያ ወይም ቅናሽ የሚያገኝ ልጅ ያላቸው እና የምግብ ድጋፍ (SNAP) የሚያገኙ ቤተሰቦች 50% ቅናሽ ይደረግላቸዋል።
- የምሳ ክፍያ ወይም ቅናሽ የሚያገኝ ልጅ ያላቸው እና በተጨማሪም እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ቤተሰቦች ጊዜያዊ እርዳታ (TANF) የሚያገኙ፣ ወይም በአሌክሳንደሪያ ከተማ ጊዜያዊ መጠለያ ውስጥ የሚኖሩ ቤተሰቦች 70% ቅናሽ ይደረግላቸዋል።
- አረጋውያን ነዋሪዎች (60 አመትና ከዚያ በላይ) በእያንዳንዱ ፕሮግራም 20% ቅናሽ ሊደረግላቸው ይችላል።
- SNAP፣ Medicaid ወይም የመኖሪያ ቤት ድጋፍ እንደሚያገኙ ማስረጃ የሚያቀርቡ አዋቂዎች 30% ቅናሽ ሊደረግላቸው ይችላል።
- የትኛውም ነዋሪ የሚፈቀድለት ከሆነ ከላይ ከተዘረዘሩት መስፈርቶች ውጭ እገዛ ሊጠይቅ የሚችል ሲሆን የድጋፉ ደረጃ በማመልከቻው ላይ ተመስርቶ ይወሰናል።
- የረጅም ጊዜ ቁርጠኝነትን የሚይዙትን ጨምሮ ልዩ ፕሮግራሞች ከላይ ከተጠቀሱት የበለጠ ደረጃ ያላቸው የፋይናንስ ድጋፎችን ሊያቀርቡ ይችላሉ፤ መረጃው በምዝገባ ሰነዶች ስር ይካተታል።

### ሥነ ሥርአቶች:

1. ነዋሪዎች ማመልከቻ ሞልተው ከደጋፊ ሰነዶች ጋር በማድረግ ለመዝናኛ ፕሮግራም ስራ አስኪያጅ/የማዕከል ዳይሬክተር ያቀርባሉ። ማመልከቻዎች በጽሁፍ ሰነድ ተደግፈው መቅረብ አለባቸው።
2. የመዝናኛ ፕሮግራም ስራ አስኪያጅ/የማዕከል ዳይሬክተር በሰነዶች ላይ ምርመራና ማጣሪያ ያደርጋል።
3. የመዝናኛ ፕሮግራም ስራ አስኪያጆች/የማዕከል ዳይሬክተሮች እንደ የመምሪያ ዳይሬክተር ተወካይ ሆነው ማመልከቻ ሊፈቅዱና ሊፈርሙ ይችላሉ።
4. የትኛውም የሚጠየቅ ከተጠቀሰው የሚለይ ወይም የሰነድ ማስረጃ የሌለው የፋይናንስ ድጋፍ በዲቪዥን ኃላፊ መፈቀድ አለበት።

## ክፍል 2 – የወጣቶች ስፖርቶች የትምህርት እድሎች የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ

**ማጠቃለያ**

RPCA በከተማ ውስጥ ለልዩ አላማዎችና ቡድኖች ግልጋሎት የመስጠትና የመዝናኛ እድሎችን የማሳደግ አላማ ይዘው የሚሰሩ የተወሰኑ ድርጅቶች እንዳሉ ይገነዘባል። እነዚህ ድርጅቶች ከከተማዋ የተለዩና እራሳቸውን ችለው የሚሰሩ ድርጅቶች ሲሆኑ የራሳቸው አመራር፣ ድርጅታዊና የአሰራር መዋቅር አላቸው።
የተገለጹት የእነዚህ ድርጅቶች ተልዕኮዎች የተለዩ ቢሆኑም እንኳ በህዝብ የመዝናኛ አገልግሎት መስጫዎችና ፕሮግራሞች ላይ ኢንቨስት ማድረግ ለሁሉም በእነዚህ ወገኖች ግልጋሎት ለሚያገኙ ግለሰቦች እና ለጠቅላላ ማህበረሰቡ ጥራታቸውን የጠበቁ የመዝናኛ እድሎች የሚቀርቡባቸው የጋራ ተጠቃሚነት አጋርነቶችን ይፈጥራሉ።

RPCA በከተማዋ የአትሌቲክስ አገልግሎት መስጫዎች የማህበረሰብ ምደባ ፖሊሲ መሰረት ከስፖርቶች ቡድን ተባባሪዎቻችን ጋር ያሉትን ጠንካራ ግንኙነቶች ያሳድጋል። RPCA አሁኑ በስራ ላይ ካሉ ድርጅቶች ጋር እንደ የሜዳና አገልግሎት መስጫዎች ምደባ፣ አጠቃቀም፣ የጊዜ ሰሌዳ በመሳሰሉ ጉዳዮች እና በአስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ ተቀራርቦ ይሰራል። የከተማዋ ተባባሪ ቡድኖች ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች በከተማዋ ውስጥ የሚቀርቡ ስፖርቶችና እድሎች አጠቃላይ አካል ተደርገው ይቆጠራሉ። በስፖርት ቡድን ተባባሪዎች እና በRPCA መካከል ያለው ግንኙነት አላማው ለከተማዋ ነዋሪዎች የአትሌቴክስ እድሎችና መዝናኛዎችን ማሳደግ ነው።

RPCA የከተማዋን ነዋሪዎች በከተማዋ ፕሮግራሞችና በተባባሪ የስፖርት ቡድኖች የተባባሪዎች ፕሮግራሞች ላይ እንዲሳተፉ ያበረታታል። የትምህርት እድሎች የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲና አሰራር የተዘጋጀው የስፖርቶች ቡድኖች የተባባሪዎች ፕሮግራሞችን ለማስቀጠልና ለማሳደግ ታስቦ ነው። የወጣቶች ስፖርቶች የትምህርት ዕድል የገንዘብ ድጋፍ ለስፖርቶች ቡድኖች ተባባሪዎች የመዝናኛ ደረጃ ፕሮግራሞቻቸው ምዝገባን ለማሳደግ ትርጉም ያለው ማበረታቻ ለመስጠት ያገለግላል።

**የገንዘብ ድጋፍ**

የወጣቶች ስፖርቶች የትምህርት ዕድል የከተማዋ ካውንስልን የአመታዊ በጀት ፍቃድና ምደባ ይጠብቃል።

**ብቁነት**

RPCA በሚከተሉት ሁኔታዎች የመዝናኛ አገልግሎት መስጫዎችና ፕሮግራሞችን በማቀናጀት ረገድ ከውጭ ለትርፍ ያልተቋቋሚ ድርጅተቶች ጋር መስራቱ የማህበረሰቡን ጥቅም እንደሚያስጠብቅ ያምናል: 1) የድርጅቱ ራዕይና አላማ ከRPCA የሚጣጣም ከሆነ፣ 2) ድርጅቶቹ RPCA ሊያቀርብ የሚችለውን አገልግሎት የሚያቀርቡ ከሆነ እና 3) ከውጭ ድርጅቶች ጋር ግንኙነቶች መፍጠሩ እያንዳንዱ ወገን የራሱን ልዩ ማንነቶች ወይም ኃላፊነቶች ሳይተው ከፍተኛ የማህበረሰብ አገልግሎት አስተዋጽኦ ማድረግ የሚችል በመሆኑ ምክንያት የህዝብ ጥቅም የሚያስገኝ ከሆነ። ብቁ የሆኑ ድርጅቶች ከከተማዋ ጋር የትብብር ስምምነት መፈራረም አለባቸው። በተጨማሪም ተባባባሪዎች ለመዝናኛ ደረጃ ፕግራሞች እኩል ተደራሽትን ለማረጋገጥ የፋይናንስ ድጋፍ ፕሮግራም ማቅረብ አለባቸው።

**ፖሊሲ**

የወጣቶች ስፖርቶች የትምህርት እድል የገንዘብ ድጋፍ በሁለት መንገዶች ይከፋፈላል፡

1. ተባባሪ የማህበረሰብ ተደራሽት ፕሮግራም
   እያንዳንዱ የስፖርቶች ቡድን ተባባሪ በእያንዳንዱ በጀት አመት ለማህበረሰብ ተደራሽነት እስከ $2,000 ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል። ተደራሽነቱ በካምፖች፣ ከሊኒኮች፣ ስዕሎች አማካኝነት ለከተማዋ ነዋሪዎች የወጣቶች ስፖርቶችን የሚያሳድጉ ወይም ከትምህርት በኋላ ፕሮግራሞችን የሚቀርብ መሆን አለበት። ተደራሽነቱ ለተሳታፊዎች በመሰረታዊ የክህሎት እድገት ላይ የሚያተኩር የመዝናኛ ደረጃ ሊግ ተሳትፎን የሚያበረታታ መሆን አለበት።

**ሥነ ሥርአቶች**

- የስፖርቶች ቡድን ተባባሪዎች ለRPCA ዳይሬክተር ወይም ተወካዩ በቀዳሚው የካላንደር አመት የፋይናንስ ድጋፍ ያገኙበትን እና መልሶ ክፍያ የሚጠይቁበትን አመት የሰነድ ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው።
- RPCA ለስፖርቶች ቡድን ተባባሪዎች በተባባሪው በሚቀርበው ደረሰኝ መሰረት መልሶ ክፍያ ይከፍላል።

**የስራ ድርሻዎችና ኃላፊነቶች**

ሁሉም የክልላዊ ፕሮግራም ዳይሬክተሮች፣ የመዝናኛ ሥራ አስኪያጆች እና በስራ ላይ ያሉ ስራ አስኪያጆች ከፊት ዴስክ ሰራተኞች ጋር በመሆን ይህ ፖሊሲ መከበሩን ማረጋገጥ አለባቸው።

**የግንኙነት መረጃ**

የዲቪዥን ኃላፊ፣ የመዝናኛ አገልግሎቶች

**ተያያዥ ሰነዶች**

የስፖርቶች ቡድን ተባባሪ ፖሊሲ